*(በአንተነህ ገብርየ)*

# ጧሪ የሌላቸውን እናቶችና አባቶች አሳዳጊ ያጡ ሕፃናትንና በሀሰት ውንጀላ ወህኒ ቤት ያጎሯቸውን የመግደል አባዜ ምን ይሉታል?

*የትግራይ ምድር ያበቀላቸው ወራሪዎች በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ጥላቻን ሰንቀው እንዲነሱ ያደረጋቸው መሠረታዊ ምክንያት ምንድን ነው?ሲባል ከሚነሱ ነጥቦች ጥቂቶቹ 1/ከሌሎች ብሔር እና ብሔረሰቦች የተለየ ጭቆና ስለደረሰባቸው፤2/የኢኮኖሚ ችግር ስለአለባቸው፤3/ ቤተሰቦቻቸው ኢትዮጵያን የሚፈታተኑ ጠላቶች በማንኛውም ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ሲዘልቁ በባንዳነት ተሰልፈው ኢትዮጵያን ያስወረሩ ያስጎረጎሩ በመሆናቸው ከድል በኋላ ከሕብረተሰቡ በመገለላቸው ቤተሰቦቻቸው ጧት ማታ ያስተማሯቸው ኢትዮጵያና ሕዝቧ የሚጠፉበትን ሴራ ነው የሚሉ ብዙ መነሻዎች ይጠቀሳሉ።*

*መጀመርያ ላይ በጠቀስኩት መሠረታዊ ምክንያት ህወሃት እንዳልተመሰረተ(አለመመሥረቱን) አምናለሁ ብዙዎቹ የሚሉትም ይኸውን ነው።ጭቆና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ትካሻ ወርዶ እንደማያውቅ ገልጽ ነው ስለዚህ የትግራይ ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለየ የደረሰበት ጭቆና አልነበረም።ከነበረ እነሆ አሁን ይህ ፀረ-ሕዝብ ድርጅት የመንግሥት ሥልጣን ከያዘ ወዲህ የትግራይ ሕዝብ አልፎለታል ማለት ነው።ሕዝቡ ከዝርፊያና ወረራ ባሻገር ሠርቶ ያለማው በላቡ ጥሮ ግሮ ያፈራው ሀብት ከሆነ እሰየው ነው።*

*በሁለተኛ ደረጃ የትግራይ ምድር ለምርት የታደለ አይደለም።በዚህ ምክንያት የትግራይ ክፍለ ሀገር ሕዝብ በኢኮኖሚ ጉዳይ የሌሎች ወይም በቀጥታ የጎንደርና ወሉ ክፍለ ሀገሮች ጥገኛ ነው።ሰፊውና አርቆ አሳቢው የጎንደር ክፍለ ሀገር ሕዝብ ደግሞ ላጣው የሚሰጥ ከእጁ ያለውን አካፍሎ የሚያድር በመሆኑ የትግራይ ሕዝብ የተለየ ጉዳት ሲደርስበት አልታየም።በተፈጥሮ አየር መዛባት ምክንያት ድርቅና ርሃብ በተደጋጋሚ ኢትዮጵያን እንደሚመታ ይታወቃል።በ1966 ዓ/ም ወሎን ያጠቃው ድርቅና ርሃብ ትግራይንም ነክቶ ሊሆን ይችላል ለጊዜው መረጃው በእጀ ስለሌለ።በ1977 ዓ/ም የተከሰተው ድርቅና ርሃብም በወሎና በጎንደር ሲከሰት በትግራይም ተከሰቷል።*

*ያ በተፈጥሮ የመጣ እንጅ ሰው ሰራሽ አልነበረም።ደርግ ያን ሁሉ የተገንጣዮች ጦርነት እየተጋፈጠ በድርቅና በርሃብ የተጎዱትን ነብስ ለማዳን በሰፈራ ጣቢታ ከቦታ ወደ ቦታ በማዛዋወር፤እንዲሁም ካያሉበት በማቅረብ እርዳታ ማድረጉ አይዘነጋም።ተገንጣይ ድርጅቶች ግን ይህን በመጠቀም የሄዱበት መንገድ ለየት ያለ ነበር።ያም አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ስለሆነ ማንሳቱ አስፈላጊ መስሎ አይታየኝም። በቀጥተኛ አነጋገር የዚህ ጉዳይ ተጠቃሽ የሚሆኑት ሻእብያና ህወሃት ናቸው እነዚህ ሁለት ድርጅቶች አንዳንዴ በመሃላቸው ስምምነት የሌለ ለማስመሰል ግጭቶችን ቢፈጥሩም ከይገባኛል ውጭ የአንድ ሳንቲም ህለት ገፆች ናቸው።*

*በሦስተኛ ደረጃ ያስቀመጥኩትን ነጥብ በሚመለከት እንደሚታወቀው በተለያዩ ጊዜዎችና ወቅቶ የኢትዮጵያ ጠላቶች በአብዛኛው የሚመጡት በሰሜን በኩል በሚገኘው የሀገሪቱ ክፍል ነው።ለዚህም የሚጠቀሙት አገር በቀል የሆኑ የኢትዮጵያ ጠላቶችን በማደራጀት በነሱ መሪነት ድምበር እየተሻገሩ አገራችን ሲያደሙ ለመኖራቸው በታሪክ ማኅደር ተመዝግቦ ይገኛል።ለአብነትም በግለሰብ ደረጃ የፀረ-ሕዝቡ ህወሃት መሪ የወራሪው ቡድን ጠቅላይ ሚንስትር የነበረው አያቱ አቶ አስረስ ተሰማ በጣሊያን የለበሱ የጎረሱ ታማኝ ባንዳ የነበሩ ሊጠቀሱ ይገባል።አንዱ ሄዶ ሌላው በመጣ ቁጥር ድል ከተመታው ወገን የነበሩ ባንዳዎች*

*ከማሕበረ ሰቡ የማግለል ሁኔታ ሲያጋጥማቸው የጠላትነት ባህርያቸው እያደገ ከእነሱ አልፎ ለልጆቻቸው በማውረስ በተለይም አሁን ያለችውን ኢትዮጵያን ከምናይበት ደረጃ ያደረሰ ጉዳይ ነው።*

*እነዚህ አናሳ ተገንጣይ ቡድኖች ኢትዮጵያን በጠላትነት ፈርጀው ሲንቀሳቀሱ ብቻቸውን አልነበሩም የውጭ ጌቶቻቸው ተገቢውን ድጋፍ እየለገሱ ከውስጥ ደግሞ ልክ ሻእቢያ ህወሃትን ህወሃት ብአዴን፤ ኦህዴድንና ደህዴድን እየፈጠሩ በኢትዮጵያ ውስጥ ጥፋቱ እየተፋፋመ እንዲሄድና አገሪቱ እንድትጠፋ ማድረግ ዓላማው በማድረግ እየተገፋ የመጣ ስለሆነ አሁን ያለው ሁኔታ ለምን ተፈጠረ ብሎ በአግራሞት መመልከት ከየዋህነት አያልፍም።በመጥፎ ልክፍት ተመርዘው ተወልደው ያደጉበትን አገር ለማጥፋትና ሕዝብን ለመጨረስ አዋጅ አውጀ በይፋ በጠራራ ፀሐይ መፍጀት ምን ያህል በውስጥ የተከፉ በመርዝ የተበከሉ ለትውልድ ግድ የማይላቸው አረመኔዎች መሆናቸውን ለዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ በደንብ አስረግጠው እየነገሩ ናቸው።የእብድ ገላጋይ ድንጋይ ያቀብላል እንዲሉ የህወሃት ጌቶችም ይህን ጸረ-ሕዝብ ቡድን አሸበሪው እርሱ፤ራሱን ከሕግ በላይ በማድረግ ለሕግ የማይገዛውና ሸፍጠኛ መሆኑን እያወቁ ድጋፍ ከመስጠት እጃቸውን የማይሰበስቡ ለምንድን ነው?የሚለው ጥያቄ ትኩረት ሊሰጠውና ይህ ፀረ-ሕዝብ ቡድን እስከ ግሳንግሱ ተጠራርጎ ሲወገድ እንደኔ የተሻለ ስአርት እናመጣለን ብየ ተስፋ አለኝ ባይመጣም ከዚህ የከፋ አይሆንም እንበልና ያኔ በዚህ ህወሃት በሚሰፍርበት መስፈሪያ የሚሰፍርላቸው እንደማያገኙ ሊያውቁትና ሊጠነቀቁ ይገባል ባይ ነኝ።የዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ፤የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፤ የአውሮፓ ህብረት፤የአፍሪካ ሕበረት፤ዓለም አቀፍ የሆኑ የሃይማኖት ተቋማት እኛ ኢትዮጵያውያን በፋሽስቱ ህወሃት በአደባባይ ስናልቅ ዝምታን የመረጡበት ምክንያት ግልጽ ነው።ይኸውም የራሳቸውን ጥቅም ማስቀደማቸው ነው።*

*እንግዲህ ህወሃት በትግራይ ጭቆና ነበር ብሎ ታገለ አልታገለ ፋይዳው የሚታየው አሁን በትግራይ ውስጥ ጭቆና መኖርና አለመኖሩ ሲመዘን ሲሆን።በኢኮኖሚያዊ ችግርና ከባንዳ ቤተሰብ በመቀዳታቸው ከጣሊአያንና ከሌሎችም ወራሪዎች የተረፈውን ትውልድ ለመጨረስ እና አገርን እስከማጥፋት ያስጨከናቸው ምንድን ነው?የሚለውን በግርድፉ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ለማቅረብ እሞክራለሁ። የያዘውን የወረወረ ፈሪ አይባልም እንዲሉ የሚሰማኝን የማሳወቅ ግዴታ ስለአለብኝ ነው።ይህ ድርጅት በ1967 ዓ/ም ሲመሰረት ከላይ ለመጥቀስ የሞከርኳቸውን ምክንያቶች መነሻ ያድርግ እንጅ ዓላማና ግቡ ጣሊያን በከፋፍለህ ግዛው መርህ አንዱን ካንዱ በማናከስ ለመግዛት ሞክሮ ያልተሳካለትን ፍላጎት ለማስፈፀም «ታላቋ ትግራይ ትግርኝት የምትባል ሪፐብሊክ» መሥርቶ ሌሎችን ቀሪ የኢትዮጵያ ግዛቶች አቅም ሲገኝ እያሰፉና የበለጠ ትግራይን እያገዘፉ መሄድ አቅም ሳይኖር ሲቀር ደግሞ ሌሎችን ሰላም እንዲያጡ እርስ በርሳቸው እየተናከሱ እንዲኖሩ ማድረግን ያለመ ሲሆን ከተገነጠለችው ኤርትራ፤ከአፋር፤ ሰሜን ጎንደርና ሰሜን ወሎ በርከት ያሉ ወረዳዎችንና አውራጃዎችን ወደ ትግራይ በመጠቅለል አዲስ አገር መስርቶ ለምኖር እንደሆነ ከራሱ ከህወሃት ማኒፌስቶ መገንዘብ ይቻላል።እዚህ ላይ ግን ህወሃቶች ሊገነዘቡት የሚገባው ነገር ቢኖር ትግራይ የማን ናት የሚለውን ታሪክ መርምረው እንዲደርሱበት ነው።*

*በኋላ ላይ በስድስተኛው ፓራግራፍ ላይ የጠቀስኩትን አንዱ ሊላውን በመፍጠር ስልት ማለትም ሻእቢያ ህወሃትን ፈጥሮ የደርግን ኃይል ከኤርትራና ትግራይ በማስወጣት መገንጠል እንደቻለው ሁሉ ህወሃት ደግሞ ኢህዴን የሚባል ቅጥረኛ በመፍጠር ወደ መሀል አገር መድረስ ችሏል።ኢህዴንም ከጌታው ህወሃት በወረደው ትእዛዝ መሠረት ደቡቦችን የስምጥ ሸለቆ፤ኦሮሞዎችን ኦህዴድ በማለት ተልእኮውን ፈጽሟል። እንግዲህ እነዚህ በህወሃት ቁመት ተለክተው የተፈጠሩ ድርጅቶችና ሌሎች አናሳ ጎሳዎችን በክልል ፈርጆ ትናንሽ ህወሃት ደፍርሶ ባደረ ቁጥር ሊቅማቸው በሚችል መልኩ የተፈጠሩ የክልል መንግሥታት ከሽግግር መንግስቱ ማከተም በኋላ በቀጥታ በህወሃት ቅኝ ግዛት ስር የወደቁና ለክልላቸው ሕዝብ ምንም ፋይዳ*

*በሌለው ሁኔታ ለ25 ዓመታት ያህል ዘልቀዋል።ይህም በመሆኑ አሁን ያለውን ሁኔታ እንደምንመለከተው በሕዝብ ላይ የተጫነው ግፍና በደል ጽዋው ሞልቶ በመፍሰሱ የሕዝብ አልገዛም ባይነት ፈንድቷል።*

*ማንነቴ ይታወቅልኝ ያለ ሕዝብ ዘሩ እንዲጠፋና እንዲፀዳ ተደርጓል፤ተሰዷል፤ሀብት ንብረቱን ተዘርፏል፤በእስር ቤት በርሃብና በድብደባ በጦርነት እንዲያልቅ ተደርጓል፤ጥሮ ግሮ በጉልበቱ ባለሰለሰው መሬት ትዳር በመሠረተበት፤ወልዶ በሳመበት፤በዳረ በኳለበት መንደሩ መኖር እንደማይችል ተደርጓል፤ለከብት ግጦሽ በከለከለው ክልክል ከብቶቹ እንዳይደርሱ ተደርጓል፤ለም መሬቱ ለጎረቤትና ለግል ባለሃብቶች ተነጥቆ ተሰጥቷል፤በጨለማው ክረምት ቤቱ ፈርሶ ሜዳ ላይ ተጥሏል፤በሃሰት ውንጀላ እስር ቤት በማስገባት በእሣት እንዲቃጠልና ሊያመልጥ ሲል መታሁት በሚል ሰበብ በህሊና እስረኛ ላይ የበቀል ርምጃ ተወስዷል፤ሕጋዊ የሆኑ የደላላ ጽ/ቤቶችን በመክፈት ሥራ ያጡ ወጣቶችን በባርነት ለዓረብ ቱጃሮችና ምዕራባውያን ሲያቀርብ፤በርሃ ላይ በውሃ ጥማትና በርሃብ በአውሬ እንዲበሉ ተደርጓል።መቸም ቢሆን የዚህን ጉደኛ ወራሪ ቡድን ጉድ ጽፎ መዘለቅ አይቻልም።እንግዲህ ይህን ሁሉ አልችልም ያለ ሕዝብ ነው ዛሬ አልገዛም ብሎ የተነሳው።ታዲያ እንዴት ጠጠር ያልወረወረ ቅጠል ያልበጠሰ ሕዝብ ተቃውሞ በማሰማቱ ግንባር ግንባሩን እየተመታ እንዲያልቅ ተፈረደበት?ከዚህ በመነሳት ነው ርእሱን ለዚህ መጣጥፌ የተጠቀምኩት።*

*እነዚህ የዛሬዎቹ ገዥዎቻችን የሩቁን እንተውና በደርግ ስርአት የመሰብሰብ ፤ሃሳብን የመግለጽ፤የመደራጀት፤የመጻፍ መብቶች መታገድ የለባቸውም በማለት ስርአቱን አውግዘው ነበር፤አስተሳሰባቸው ከአፍንጫ እስከ ዐይን ያለውን ያህል ባይርቅም ስለዴሞክራሲ ሰብከው ነበር፤በትግራይ እናቶችና አባወራዎች ሞት ምክንያት፤ድርቅ ባስከተለው አደጋ የነበረው መንግሥት ኃላፊነት የጎደለው ነው ብለዋል።ታዲያ አሁን በመላ ኢትዮጵያ የድርቅና የርሃብ አደጋ ሲያንዣብብ ወደ መሀል ገብቶ ችግሩን ከመጋፈጥ ይልቅ በዚህ ዙርያ ያለውን እሳቤ ለማስፈንጠር በአዲስ አበባ አካባቢ የመሬት መስፋፋት፤በሰሜን ጎንደር በወልቃይት የአማራ ብሔር ማንነትን ጉዳይ ቁልፍና ወቅታዊ ጉዳይ ሆነውና ለ25 አመታት ያህል በሕዝቡ ውስጥ ተረግዞ የነበረውን አፈና የመብት ረገጣ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ወንጀል ሆኖ በዜጎች ላይ የተደረገው ግፍና በደል ገንፍሎ ሲወጣ ነብሰ ጡር፤ታዳጊ ወጣቶችና ጧሪ በሌላቸው ወላጆች ላይ አልሞ ተኳሽ በማሰማራት የጅምላ እልቂት የሚፈጽምን ምን ይሉታል?አሸንዳ በአል ትልቅ ቦታ ተሰጥቶት በመንግስት ወጭ ሲከበር ኦሮሞዎቹ የገዳ ስርአት በአላቸውን ለማክበር(የእሬቻ በዓልን) በቢሸፍቱ ጮፌና አድዮ አበባ ይዘው ሲወጡ በአየርና በእግረኛ በተተኮሰ ጥይትና በመርዝ ጭስ ለምን እንዲያልቁ ተፈረደ?ይህ ወራሪ ቡድን የኢትዮጵያን ሕዝብ ሊመራ ወይም ሊያስተዳደር ወይንስ ጨርሶ ሊያጠፋ የመጣ ነው?*

*ጌቶቻችን እስከ ዛሬ አንዱን ከአንዱ ጋር በማቃረን እልቂት ፈጽመዋል ብዙውን በማይታወቅ መንገድ በስውር አጥፍተዋል፤በሰበብ አስባቡም በይፋ ገድለዋል።በአጠቃላይ ለ25 አመታት ያህል ያለ አዋጅ ሲገድሉን ኖረዋል አሁን ደግሞ ጸጥ ረጭ ብለን እንድንገዛ፤እንዳንተነፍስ፤እንዳንቀሳቀስ፤ጨረቃና ፀሐይም እንዳናይ የሚከለክል አዋጅ ወጥቶልናል እኒህ ታዲያ ሰውአዊ ፍጡር ናቸው ወይስ አራዊቶች?ያላችሁትን በሏቸው መልሱን ለእናንተው ትቸዋለሁ።በአዋጅ እንድናልቅ መደረጉ ግን የተሻለ ይመስለኛል።ጉዳዩንና ሟቹን የሚያውቀው አንዱ አምላክ የፈጠረን ጌታ ስለሆነ ሁሉንም እናያለን።*

*በመጨረሻም የዚህ ሁሉ ችግር መንስኤው ህወሃት ቢሆንም የእኛም አስተዋጽኦ ትልቅ ሚና እንደተጫወተ በማመን ተቀብለን መፍትሔውን ልንፈጥር መቻል ይገባናል።አንድ በህወሃት ቤት የማይወደድ በጣም የሚጠሉት ነገር አለ እሱም አንድነት ነው።ለአንድነት ፍጥነት በሚሰጠው መልኩ መደራጀቱ አስፈላጊ ቢሆንም የጋራ ለሆነችው አንዲት ኢትዮጵያና አንድ ሕዝብ ተገዥ በመሆን የዜጎች መብት በእኩልነት የሚከበርበትን፤የሕግ የበላይነት የሚነግስበትን፤ሰላም የሚሰፍንበትንና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚመጣበትን መንገድ በጋራ ለማምጣት በጋራ መቆም የግድ ይለናል።በቅርቡ በአማራና ኦሮሞ*

*ወንድማማቾች መሀከል የነበረውን መቃቃር ሰብሮ በመውጣት በህወሃት መንደር የተፈጠረውን መርበትበት ተመልክተናል ስለዚህ ይህ አይነቱ ትብብር ሊያድግና ሊጠናከር ይገባዋል።*

*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!*

*ሞት ለትግራይ ወያኔ !!*